ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭፣ ጥር ፳፻፲፫ ዓ.ም

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።



ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያ የተገጣጠመ የኤሌክትሪክ መኪና ከሃዩንዳይ ማራቶን ሞተርስ ሲረከቡ

በዚህ እትም. . .

ለኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ ዕቅድ ስኬት የትራንስፖርት ዘርፉ ድርሻ ፪

ዜናዎች ፪

የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመከላከል በኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሠረት አድርገው የተሠሩ የማጣጣሚያ ስራዎች አጠቃላይ ዕይታ ፫

ሁነቶች ፭

ልዩ ልዩ ህትመቶች ፮



ዋና አዘጋጅ፥ ንጉሱ ለማ ገብሬ

አዘጋጆች፥ ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

አምደኞች፥ መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

ግራፊክስና ሌይአውት፥ አርሴማ አንዳርጋቸው

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

ዜናዎች

ኢትዮጵያ የተሻሻለውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ አስረከበች

በታህሳስ 22, 2013 ኢትዮጵያ የተሻሻለውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ማጠቃለያ አቅርባለች። የቀረበው የዕቅዱ አፅርኦተ ሀሳብ የዕቅዱን የአፈፃፀም ስልት ያካተተና በዕቅዱ የተለዩ የማጣጣሚያና ማስተሰርያ አማራጮች ያካተተ ነው። በተጨማሪም ለአማራጮቹ መተግበሪያ፣ ዘገባ ለማቅረብና ለማረጋገጥን እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ስርዐትን ለመዘርጋት የሚያስፈልጉ ሀብቶችን ያመላክታል። ምንጭ

አሜሪካ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ቁርጠኝነቷን የሚያድሱ እርምጃዎችን ወሰደች

ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን በፌደራል መንግስት ደረጃ የሚተገበር የአየር ንብረት ለውጥን ለቋቋም የሚረዱና በግንባር ቀደም አጀንዳነት ተግባራዊ የሚያደርጉ እርምጃዎችን ስራ በጀመሩባቸው የመጀመሪያዎቹ ሰባት ቀናት ወስደዋል።

የፕሬዝዳንት ባይደን እርምጃ የአየር ንብረት ለውጥን በሀገር ውስጥ ተቀዳሚ ፖሊስ ከማድረግ በተጨማሪ ጉዳዩ የአሜሪካ ቁልፍ የደህንነትና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማጠንጠኛ እንዲሆን አድርጎታል። ምንጭ

በተመሳሳይ ሁኔታ የተ.መ.ድ. የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ዋና ፀሀፊ የሆኑት ወ/ሮ ፓትሪሽያ ስፒኖሳ ለሮይተርስ እንደተናገሩት 'በዓለማቀፍ የዓየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ወቅት አሜሪካ ለፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት አዎንታዊ ሚና ተጫውታለች፣ በመሆኑም ተመሳሳይ የመሪነት ሚናን እንጠብቃለን' ብለዋል። ክብርት ስፓኞሳ በመልዕክታቸው አክለውም ባለፀጋ ሀገራት እ.አ.አ. በ2009 ቃል የገቡትን እ.አ.አ. በ2020 ታዳጊ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርስባቸውን ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚረዳቸውን የ100 ቢሊዮን ዶላር ዓመታዊ ድጋፍ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል። በቅርቡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በወጣ መረጃ መሠረት ያደጉ ሀገራት ዓመታዊ ግቡን ከማሳካት አኳያ እ.አ.አ. በ2018 የ21 ቢሊዮን ዶላር ጉለት ተስተውሏል።

ለኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ ዕቅድ ስኬት የትራንስፖርት ዘርፉ ድርሻ

- ጆቢር አያሌው፣ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ዳይሬክተር

የትራንስፖርት ዘርፍ በሰዎች ዝውውር በኢንቨስትመንት ፍሰትና የምርተቶች እንቅስቃሴ ላይ ጠቃሚ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ነው። ውጤታማ የትራንስፖርት ስርዐት በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድሎችንና ጥቅሞችን ለምሳሌ የተሻሻለ የገበያ እድል፣ የስራ እድል እና የኢንቨስትመንት እድሎችን ይሰጣል። በሌላ በኩል ከአቅምና አስተማማኝነት አኳያ ውጤታማ ያልሆነ የትራንስፖርት ስርዐት በርካታ እድሎችን የሚያሳጣና የኑሮ ደረጃን ዝቅ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ዘላቂ፣ ትክክለኛና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት ስርዐት መዘርጋት የተጣጣመ ኢኮኖሚያዊ ምህዳርና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ እንዲኖር ያስችላል።

ይሁንና በአሁኑ ወቅት የትራንስፖርት ዘርፍ ለዓለማቀፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ከፍተኛ አስተዋጽዎ ካላቸው ዘርፎች መሃከል ሲሆን ይህም ለዓለማቀፍ የሙቀት መጠን መጨመርና ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ነው። "ዘላቂና አነስተኛ የትራንስፖርት ዘርፍ የበካይ ጋዞች ልቀት ሽርክና" እንደተባለ ድርጅት ዘገባ የዓለማቀፍ የትራንስፖርት ዘርፍ 'የካርቦን ዳይኦክሳይድ' ቀጥተኛ ልቀት እ.አ.አ. በ2000 እና 2016 መካከል ብቻ በ29% ያደገ ሲሆን ይህም ከ5.8 ጊጋ ቶን ወደ 7.5 ጊጋ ቶን የጨመረ መሆኑን አረጋግጧል። በዚህም ወቅት በዓለማችን ከሀይል ጋር ተዛማጅ የሆኑ የካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀቶች 23% ያህሉ ከዚህ ዘርፍ ብቻ የመጣ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ እ.አ.አ. በ2018 የዓለምዓቀፍ 'የሀይል' ኤጀንሲ እንዳወጣው ዘገባ እ.አ.አ. በ2017 የትራንስፖርት ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋሶች ልቀት መጠን 5.3 ሚሊዮን ቶን የካርቦን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ ነበር። በተመሳሳይ እ.አ.አ. ከ2011 ጀምሮ ትግበራ ላይ የሚገኘው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልትና እ.አ.አ. በ2015 ይፋ የሆነው የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ እንደሚያመላክቱት እ.አ.አ. በ2010 የትራንስፖርት ዘርፍ የልቀት መጠን 5 ሚሊዮን ቶን የካርቦን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ ነበር፤ ይህም ከኢትዮጵያ ጠቅላላ የሙቀት አማቂ ጋሶች ልቀትን መጠን 3% ያህሉን ይሸፍናል። ይህም ማለት በተለመደው አኳኋን ከተሄደ እ.አ.አ. በ2030 40 ሚሊዮን ቶን የካርቦን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ ይደርሳል።

ወደ ገፅ ፫

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

ከገፅ ፪ የቀጠለ..

በዘርፉ የሚታየው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ጭማሬ የሚስተዋለው በዋነኛነት ከእቃ ማመላለሻ (+13% p.a.) እና ከመንገደኞች (+9% p.a.) ትራንስፖርት ነው።

ዝቅተኛ የካርቦን ልቀት ያላቸውን የትራንስፖርት አማራጮችን መጠቀም ሌሎች የትራንስፖርት ሀይል አማራጮችን ከመጠቀም በዝቅተኛ ዋጋ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ የሚያስችል ስልት ነው። ይህም ስልት የጉዞ መጠንን መቀነስ፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን የትራንስፖርት አማራጮችን አብዝቶ መጠቀም፣ የተሻሻለ የትራንስፖርት አስተዳደር ስርዐቶችን ተግባራዊ ማድረግና ውጤታማ ያልሆኑና የተጨናነቁ የትራንስፖርት አማራጮችን ማስወገድን ያካትታል። ከዚህም በተጨማሪ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልትም ሆነ የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ እንደሚያመላክቱት በኢትዮጵያ የትራንስፖርት ዘርፍ የዘርፉ ቴክኖሎጂዎች ትግበራ ላይ እመርታዊ ለውጥ ማድረግ ከዘርፉ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በግምት እስከ 13.2 ሚሊዮን ቶን እ.አ.አ. 2030 የመቀነስ አቅም አለው። ይህ ውጤት ሊገኝ የሚችለው ደግሞ በዘርፉ አዳዲስ እርምጃዎችን ማለትም እንደ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ዝርጋታ፣ ፈጣን የከተማ አውቶቡሶች ስምሪትን መተግበር፣ የተሻሻሉና ነዳጅ ቆጣቢ ተሽከርካሪዎችን ወደ መንገድ ማስገባት ከተቻለና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎትን ወደ ኤሌክትሪክ ሀይል አማራጭ ማሸጋገር ከተቻለ ነው።

ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎች ቅነሳ የትራንስፖርት ዘርፍ ቁልፍ ምላሾች

በኢትዮጵያ የትራንስፖርት ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ ተቀይሰው በመተግበር ላይ ከሚገኙ ስልቶች አንዱ ለሰዎችና ለጭነት ማጓጓዣ የሚያገለግሉ የትራንስፖርት አማራጮችን የሀይል አማራጭ በታዳሽ ሀይል መተካት ነው። ካሉ የሀይል አማራጮች በተለየ ሁኔታ ደግሞ የሰውና የጭነት ተሽከርካሪዎችን ከነዳጅ ወደ ኤሌክትሪክ ሀይል የትስስር አማራጭ መቀየር ነው። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ 34.25 ኪሎ ሜትር የቀላል ባቡር መሸጋገሪያ ስርዐት በአዲስ አበባና 656 ኪሎ ሜትር የኤሌክትሪክ ባቡር መስመር ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ዘርግታለች። ከዚህም በተጨማሪ ከአዋሽ እስከ መቀሌ የሚዘልቅ የ609 ኪሎ ሜትር የባቡር መሠረተ ልማት መስመር በግንባታ ላይ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት በቀን ለ 94,160 መንገደኞች አገልግሎት የመስጠት አቅም ያለው ሲሆን ባለፉት አምስት ዓመታት በድምሩ 169.5 ሚሊዮን መንገደኞችን አገልግሏል። በሌላ በኩል እ.ኤ.አ. በ 2019/2020 የአዲስ አበባ - ጅቡቲ የኤሌክትሪክ ባቡር ወደ 79,360 ለሚጠጉ ተሳፋሪዎችና 1.4 ሚሊዮን ቶን ሸቀጣ ሸቀጦችን አገልግሎት ሰጥቷል።



ኢትዮ ጅቡቲ የባቡር መስመር

ሞተር-አልባ ተሽከርካሪዎችን ለማበረታታት እና የአየር ብክለትን ለመቀነስ የትራንስፖርት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ በየወሩ የመጨረሻ እሁድ የሚከናወን ወርሃዊ ከመኪና ነፃ የሆነ ቀን ጀምሯል ። በተጨማሪም የትራንስፖርት ሚኒስቴር በቅርቡ በአገሪቱ ውስጥ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሠረተ ልማትና አገልግሎት መገንባት አስፈላጊ መሆኑን የሚያጎላ የትራንስፖርት ፖሊሲ አውጥቷል ። በተጨማሪም የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን የመቋቋም አቅም ለመገንባት እና ከዘርፉ የሚለቀቀውን ልቀት ለመቀነስ ሞተር-አልባ ትራንስፖርትን በተመለከተ እና የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚያስችሉ የትራንስፖርት ዘርፍ ስትራቴጂዎች እ.አ.አ. በ 2018 እና በ 2020 በቅደም ተከተል ወጥተው በትግበራ ላይ ይገኛሉ።

ከትራንስፖርት ዘርፉ የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን በለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት እና በኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ቅነሳ ዕቅድ ውስጥ በተቀመጡት ደረጃዎች መሠረት እንዲቀንስ ለማድረግ የተለያዩ ውጥኖች እየተከናወኑ ናቸው ። የግሉ ዘርፉ ተሳትፎ በተለይ የዘርፉን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች ለመቋቋም የወጣውን ፖሊሲ ለማሳካት አስፈላጊና ጠቃሚም እንደሆነ ታምኖበታል ። በዚህ ረገድ ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል ተሽከርካሪ መሸጋገሩን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኙት ማራቶን ሞተርስ እና ቶም ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ የተሠኙ የግል ሴክተር ኩባንያዎች የትራንስፖርት አቅርቦቱ በካይ የሀይል አማራጮችን ከሚጠቀሙ የትራንስፖርት አማራጮች ወደ የኤሌክትሪክ ሀይልን ወደሚጠቀሙ የትራንስፖርት አማራጮች በማሸጋገር ረገድ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

ወደ ገፅ ፬

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

በአዲስ አበባ ከተማ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ አውቶቡሶችን የማስጀመር እንቅስቃሴ

❑ ፍሰሃ ፈንታሁን፤ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የፈጣን አውቶቡስ ትራንስፖርት ፕሮጀክት ልማትና ጥናት ቡድን መሪ

አዲስ አበባ እንደ በርካታ የአፍሪካ ከተሞች ሁሉ በየአስር ዓመቱ በህዝብ ቁጥር ብዛት በፍጥነት እየጨመረችና በስፋትም በእጥፍ እያደገች ነው። በአሁኑ ወቅት የትራንስፖርት ዘርፍ የከተማዋን አጠቃላይ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን 68% ያህል የሚሸፍን ሲሆን በዚህ ሳቢያ በከተማዋ የአየር ብክለት ለሞት ከሚዳርጉ ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው ።

ለዚህ ተግዳሮት ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድም ኢትዮጵያ ወደ ዘላቂ የህዝብ ማመላለሻ አማራጮችን ለማስፋፋት በትኩረት እየሠራች ነው። አሁን ተግባራዊ እየሆነ በሚገኘውና እ.አ.አ.2017-2027 በመተግበር ላይ በሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን ዕቅድ መሠረት የሁለት የፈጣን አውቶቡስ ማሳለጫ ኮሪደሮች ልማት በግንባታ ላይ የሚገኙ ሲሆን ይህም በዕቅድ ዘመኑ ሊተገበሩ ከተያዙ 15 ኮሪደሮች ውስጥ የተካተተ ነው።

እስካሁን ባለው ጊዜ ለአዲስ አበባ የፈጣን አውቶቡሶች ግዢ ጨረታ ወይም ግዥ ያልተከናወነ በመሆኑ ጭስ አልባ አውቶቡሶች ማለትም በባትሪ-ኤሌክትሪክ የሚሰሩ አውቶቡሶችን ወደ ፈጣን የአውቶቡስ ማሳለጫ መስመሩ ለማስገባት ለአዲስ አበባ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚወሰድ ነው። ይህም ከተማዋን በናፍጣ ነዳጅ ተጠቃሚነት ምክንያት ከመኪኖች ጭስ በሚወጣ የአየር መበከል በቀጣይ ከ 20 በላይ ዓመታት ሊያጋጥማት ከሚችለው ማነቆ ነፃ ያደርጋታል።

ይህንን ምኞት ለመደገፍ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ከ ሲ40 ሲቲ ሶሉሽንስ ፕላትፎርም ጋር በመተባበር በበይነ መረብ ከግል፣ ከመንግሥት፣ ከትምህርት ተቋማት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተዋንያን ጋር ትብብርን በማመቻቸት በመስራት ላይ ይገኛል። ይህም ጥረት እያደገ የሚሄድና ተጨባጭ የሆኑ ሀሳቦችን እና መፍትሄዎችን ለማዳበር የሚረዳ ነው። በዚህ ጥረት ላይ ሲ.ዲ.ኬ.ኤን. (CDKN) ከ ሲ40 (C40) ጋር ጥምረትን በመፍጠር የሰራ ሲሆን፣ ስራውም ከኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋምና የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ ሲሆን የፓሪስ ስምምነት ግቦችን ለማሳካት አዲስ አበባ ከተማ በትክክለኛ መስመር ላይ መሆኗንም የሚያረጋግጥ ነው።

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ከሲ-40 ጋር በመተባበር በበይነ መረብ ተደግፎ በተካሄደው ሁነት ውይይት ወቅት የተነሱ ገንቢ የመፍትሄ ምክረ ሀሳቦችን በመገምገምና በመተንተን እንዲሁም ከከተማዋና ከሀገሪቱ ትልሞች ጋር በማጣጣም ከተማዋን ከትራንስፖርት የአየር ብክለት ነፃ ለማድረግና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በመተካት ንፁህ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ዘላቂነት ያለው እንዲሁም ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል የትራንስፖርት ስርዐት ለመዘርጋት እየሠራ ነው። ሙሉ ዘገባ ያንብቡ

ከገፅ ፫ የቀጠለ

የትራንስፖርት ዘርፍ የቀጣይ አስር ዓመታት መሪ የልማት ዕቅድ

የኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልትም ሆነ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ እንደሚያመላክቱት ወደ ዘመናዊ እና ሀይል ቆጣቢ የቴክኖሎጂ አማራጮች መሸጋገር ለዘርፉ የአየር ንብረት ለውጥ መከላከል እንደ እምቅ አቅም የሚወሰድ ነው። ከዚህ በመነሳት በትራንስፖርት ዘርፉ እ.ኤ.አ. 2020/21 - 2029/30 በቀጣይ አስር ዓመታት የሚከናወነው መሪ የልማት ዕቅድ ለኢትዮጵያ ህዝቦች እና ለአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነትን ከፍ የሚያደርግ፣ ተመጣጣኝ፣ የተቀናጀ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምላሽ ሰጭ እና ቀጣይነት ያለው የትራንስፖርት ስርዓት መዘርጋትን ዒላማ ያደረገ ነው።

የዘርፉ እቅድ 25 ኪ.ሜ የኬብል ትራንስፖርት መሰረተ ልማት መዘርጋትን፣ 7 ፈጣን የአውቶብስ ትራንስፖርት መዳረሻዎች መገንባትን፣ 3,309 ኪ.ሜ አዲስ የባቡር መሰረተ ልማት መገንባት እና የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ባቡር መሰረተ ልማት ወደ 4,199 ኪ.ሜ ከፍ ማድረግ፤ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎትን ለ648.6 ሺህ ተጠቃሚዎች እና ለ5.96 ሚሊዮን የጭነት አገልግሎቶች ተደራሽ ማድረግን ያካትታል። በተጨማሪም በ 69 ከተሞች ውስጥ 506 ኪ.ሜ ያህል የእግረኞች እና የብስክሌት ተሽከርካሪ መሰረተ ልማቶችን ለመገንባት እና 4,850 የኤሌክትሪክ አውቶቡሶችንና 148,000 የኤሌክትሪክ መኪናዎችን እ.አ.አ. በ 2030 ለማቅረብ አልሟል።

የዚህ እቅድ ትግበራ እውን ሲሆን በሀገራችን የከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርሻ ከ 34% ወደ 70% ከፍ ያደርገዋል ተብሎ ይጠበቃል። ይህ መሆኑ ደግሞ በዘርፉ በአጠቃላይ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በ13.9 ሚ.ሜትሪክ ቶን እኩሌታ ይቀንሳል።በዚህ እቅድ አፈፃፀም የግሉ ዘርፍን ከፍተኛ ተሳትፎ ለማረጋገጥ በተለይም ነዳጅ ቆጣቢ የሆኑና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ትኩረት ለመስጠት የተለያዩ የማበረታቻ ዘዴዎች ይቀረጻሉ።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተካሄዱ ናቸው። የሚከተሉት በበይነ መረብ አማካይነት የሚከናወኑ ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- ከቃላት በላይ፤ ግሀዱ የአየር ንብረት ለውጥ ታሪክ በምስል፣ ክላይሜት ዋን፣ መጋቢት 2021| ምንጭ
- ካርታ አዘጋጅ፤ ሊጣጣም የሚችልና ለመሬት አጠቃቀም ቁጥጥር የሚያገለግል መሳሪያ፣ ደብልዩ. አር. አይ.፣ መጋቢት 2021 | ምንጭ
- ሲሪዝ 2021- ነገን በዛሬ ጥረት ማሸጋገር፣ ሲሪዝ፣ መጋቢት 2021 | ምንጭ
- መረጃና ዲዛይን፤ ታሪኮችን እንዲታዩ ማድረግ፣ ኦ.ዲ.አይ፣ መጋቢት 2021 | ምንጭ
- የዘላቂ የልማት ግቦች ፋይናንስ የጀኔቫ ጉባኤ 2021፣ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- 9ነኛው ዓለማቀፍ የስነ-ምዳር ጥበቃ ኮንፈረንስ፣ ማህበረሰብ ለስነ-ምዳር ጥበቃ ማህበር፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፤ ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሰኔ 2021| ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፤ ውቅያኖሶችና ውሀ-ወለድ ኢኮኖሚ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፤ የመሬት አጠቃቀምና እርሻ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሰኔ 2021 | ምንጭ
- የአየር ንብረት የፈጠራ መድረክ 2021 ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ

የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመከላከል በኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሠረት አድርገው የተሠሩ የማጣጣሚያ ስራዎች አጠቃላይ ዕይታ

❑ **በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የተዘጋጀ**

ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች፤ ተያያዥና ተደራራቢ የሆኑ ከአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ እስከ ብዝሀ ህይወት መመናመን ያሉ የአካባቢ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ የሆነ አቅም እንዳላቸው ተቀባይነት እያገኙ መጥተዋል። የአየር ንብረት ለውጥ ቀውስን በተመለከተ ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች የሙቀት አማቂ ጋዝን ለመቀነስና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለማጣጣም እስከአሁን በበቂ ያልተጠቀምንበት አቅም አላቸው። በ2019 እ.አ.አ የወጣው የአለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ኮሚሽን ሪፖርት መሰረት፤ ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎችን መተግበር፤ አንድ ሶስተኛ የሚሆነውን የማስተሰረያ ዒላማ በ2030 እ.አ.አ በማሳካት የአለም የአየር ሙቀትን በ2°C ለመቀነስ ለሚደረገው ጥረት አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቅረፍ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በብሄራዊና አለም አቀፍ ፖሊሲዎች ላይ ትኩረትን አላገኘም፣ በአግባቡ አልተተገበረም ከዚህ በተጨማሪ ለትግበራውም በቂ ፋይናንስ አልተመደበለትም። በተጨማሪም ለአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ያላቸውን ጠቀሜታ ወደጎን በመተው ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች ላይ የተካሄዱ ውይይቶች የሚያተኩሩት ለማስተሰረያ ያላቸው አቅም ላይ ብቻ ነው። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) የ2021 እ.ኤ.አ የማጣጣሚያ ስራዎች ክፍተት ሪፖርት ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች ለአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ያላቸው መፍትሄ ላይ መተኮር እንዳለበት አመላክቷል።


ይህ ፅሁፍ መሰረት ያደረገው “የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመከላከል በኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሠረት አድርገው በተሠሩ የማጣጣሚያ ስራዎች” በሚል ርዕስ በአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽንና የአለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ኮሚሽን በጥምረት በታህሳስ 2020 ባካሄዱት የውይይት መድረክ ሪፖርት ላይ ነው። ፅሁፉ የኢትዮጵያን ተሞክሮ በማካፈል ተፈጥሮን መሠረት አድርገው በተሠሩ የማጣጣሚያ ስራዎች ዙሪያ በአለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ ላሉ ውይይቶች አስተዋጽኦ ለማድረግ ሞክሯል። ይህንንም ለማድረግ ተፈጥሮን መሠረት አድርገው በኢትዮጵያ ባለፉት አስር አመታት የተሠሩ የማጣጣሚያ ስራዎች ልምድን ጠቅለል ባለ ሁኔታ ይዳስሳል። **ወደ ገፅ ፮**

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭


ልዩ ልዩ ሀትመቶች

በዘመነ ኮቪድ-19 የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስን ማሳደግ




ይህ የአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ (GCF) የዳሰሳ ጥናት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ውስጥ አነስተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚጣጣሙ ኢንቨስትመንቶችና የፋይናንስ ተደራሽነት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በመገምገም የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስን ለማሳደግ የፖሊሲ፣ የፋይናንስ እና የተቋማት ታላላቅ ቅንጅቶችን የዳሰሰ ነው። ምንጭ

በተመድ. የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት አሰራር መሠረት ሀብት ለማፈላለግ የሚረዳ የኪስ መመሪያ



ፋይናንስ በአለም የአየር ንብረት ለውጥ ድርድሮች ውስጥ የተግባራዊነት እርምጃዎች ማሳያነት ሆኖ ከማገልገሉም በተጨማሪ በበለፀጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል ያለው የመተማመን ደረጃም የጠቋሚነት ሚና ይጫወታል። የዚህ የኪስ መመሪያ ዓላማም የታዳጊ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ተደራዳሪዎች በጉዳዩ ዙሪያ ያለውን ውስብስብነት እንዲረዱና ለወደፊቱ የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲደራደሩ ይረዳል ። ምንጭ

የአየር ንብረት ለውጥን በሚቋቋም መንገድ ለማገገም ዘላቂነት ያላቸው የማቀዝቀዣ ዘዴዎችን መጠቀም



ይህ አጭር መግለጫ በብዙ ወሳኝ የኢኮኖሚ ዘርፎች ወይም ስርዓቶች የሀገራት መንግስታት ፖሊሲያቸውን እንዴት ማስተካከልና የማቀዝቀዣዎችን ተጠቃሚነትን በአማራጮቻቸው ውስጥ ማካተት እንደሚችሉ ያሳያል። ምንጭ

ከገፅ ፭ የቀጠለ...

ሀገራዊ ሁኔታና ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች

በፖሊሲ ደረጃ ኢትዮጵያ ተፈጥሮንና ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች አካባቢ ላይ የሚደርሱ ችግሮችን ለመቅረፍ ላላቸው ሚና ከፍተኛ ዕውቅና ሰጥታለች። የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ውስብስብ የአካባቢ ችግሮችን እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቅረፍ ለሚኖራቸው አስፈላጊነት አፅንዖት ይሰጣል። በተመሳሳይ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን መሰረት አድርገው የተሰሩት የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC) እና ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ (NAP) ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ለአየር ንብረት ማጣጣሚያነት ያላቸውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ሰጥቷል።

እነዚህ ተግባራት የደን ጥምር እርሻን ከማስፋትና ዘላቂ ደን ልማት በተራቆቱ ስፍራዎች ላይ ከማካሄድ እስከ የስርዐተ-ምህዳርን ጤናን በስርዐተ-ምህዳራዊ የአስተራረስ ዘዴ ማሻሻል ድረስ ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪም የአፈር መሸርሸርን የሚከላከሉ፣ የውሀን መጠን የሚጠብቁና የዕፅዋትን ሽፋን የሚጨምሩ የዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ተግባራትን ሲያጠቃልል በተጨማሪም የስርዐተ-ምህዳር፣ የማህበረሰቡንና የመሰረተ ልማቱን አየር ንበረት ለውጥን የመቋቋም ችሎታ ስርዐተ-ምዳራዊ በሆነ መንገድ መጠበቅን ይመለከታል። በተመሳሳይም በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዘዴ ስር የተለዩት ተግባራት ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ የአየር ንብረት ማጣጣሚያዎችን አካተዋል። ይህም በጥቂቱ ለመግለፅ ያህል የግብርና ምርትን ለአየር ንብረት ተስማሚ በሆነ ትግበራ መንገድ በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ መሬትንና የውሀ ተፋሰስን በመጠበቅ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን ማጠናከር፣ ብዝሀ-ህይወትን በመጠበቅ የስርዐተ-ምህዳር አልበገሬነት ማረጋገጥን ያካትታል።

ስኬቶች

ከላይ በተጠቀሱት የብሄራዊ ፖሊሲ ጉዳዮች መሰረት፤ በተለይም ለአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ የሚሆኑ ያጠቃልላል፤ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎችን ኢትዮጵያ ስትተገብር ቆይታለች። እነዚህ ተግባራትም የተራቆቱ ቦታዎች መልሰው እንዲያገግሙ ከማድረግና አረንጓዴ እንዲሆኑ ከማስቻል እስከ ዘላቂ በሆነ መንገድ መሬትን፣ ውሀና የደን ሀብትን በመጠበቅ የህብረተሰቡን፣ የአካባቢንና የኢኮኖሚውን የመቋቋም ችሎታ ማሳደግና አልበገሬነትን መገንባትን ያካትታል። ወደ ገፅ ፮

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፩

ከገፅ ፮ የቀጠለ...

በመከናወን ላይ የሚገኙ ዋና ዋና ተግባራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን


ሀ. **የተራቆቱ መሬቶችን እንዲያገግሙ ማስቻል**

የተራቆቱ መሬቶችን እንዲያገግሙ የማድረግ ስራ ዋነኛ የኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ የማጣጣሚያ መፍትሄዎች መገለጫ ሁኖ ቆይቷል። ኢትዮጵያ 15 ሚሊዮን ሄክታር የተራቆተና የተጨፈጨፈ ደንን ለማልማት ለአፍሪካ የደን መሬት የማገገም ትግበራ (AFR100)፣ ለቦን ቻሌንጅ፣ እንዲሁም ለኒውዮርክ ዲክላሬሽን ቃል የገባች ሲሆን ይህም በአለም ከፍተኛው ነው። ኢትየጵያ የተጎዱ መሬቶችን እንዲያገግሙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ተሞክሮ አላት። ለዚህም ስኬት ዋነኛ ምክንያቱ ባለፉት አስርት አመታት ለዚህ ስራ የተሰጠው የመንግስት ከፍተኛ ቁርጠኝነት ነው። ሀገሪቱ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎችን እና የደን ልማትን በማካሄድ የተራቆቱ መሬቶች እንዲያገግሙ ለማስቻል በሚሊዮን የሚቆጠር የማህበረሰብ ክፍል እንዲካፈል አድርጋለች።

ከዚህ በተጨማሪ የመሬት መራቆትን ለመቀነስና ምርታማነትን ለመጨመር የኢትዮጵያ መንግስት የዘላቂ መሬት አስተዳደርን ተከትሏል። የዘላቂ መሬት አስተዳደር ፕሮግራም ዓላማን ለማሳካት ሶስት ተከታታይ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ሲተገበሩ ቆይተዋል። የመጀመሪያዎቹ ሁለት የፕሮጀክት ምዕራፎች በከፍተኛ ሁኔታ በተራቆቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የዘላቂ መሬት አስተዳደርና አፈፃፀርን የሚያሻሽሉ ስራዎች እንዲተገብሩ በማድረግ ከ1,200,000 ሄ/ር በላይ የተራቆተ መሬት ለማሻሻል ተችሏል። አሁን እየተተገበረ ባለው ሶስተኛ ምዕራፍ (2019-2024) 1,581,000 ሄ/ር ለመሸፈን ታቅዷል። በዚህኛው ምዕራፍ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማህበር በእያንዳንዱ ተፋሰስ ማቋቋም፣ እንዲያገግሙ ለሚደረጉት ተፋሰሶች የመሬት አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድን ማዘጋጀት፣ እንዲሁም የማህበራቱን የዕውቀት አስተዳደርና የመረጃ አያያዝ ዘዴን ለማዘመን ታቅዷል።

ኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሰረት ላደረጉ መፍትሄዎች ያላትን ቁርጠኝነት የአንጓዴ አሻራ ፕሮግራምን ይፋ በማድረግ አሳይታለች። በዚህ ፕሮግራም ከ20 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በ4 ዓመታት ውስጥ ለመትከል የታቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ባለፉት 2 ዓመታት 9 ቢሊዮን የሚሆን ችግኝ ለመትከል ተችሏል። ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ መተግበር የመሬት መራቆትን በመቀነስ የህብረተሰቡን የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ችሎታውን ለማሳደግ፣ የተራቆቱ መሬቶች ወደነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ፣ የተፋሰስ ሀይድሮሎጂንና የአፈር ለምነትን በመጨመር የስርዐተ-ምህዳሩን ጤና ለማረጋገጥ እና የማህበረሰቡን የኑሮ ዘዴ ለማሻሻል ይረዳል።

ወደ ገፅ ፭







በጉራጌ ዞን፣ ጉመር ወረዳ የፉሲርባድ አነስተኛ ተፋሰስ ጠረጴዛማ እርከን ስርዓት ቅድመና ድህረ ገጽታዎች፤ ዘላቂ የመሬት አስተዳደር ፕሮግራም

ከገፅ ፮ የቀጠለ...

የኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ትግበራ ከተሞችን በአረንጓዴ መሸፈንን ያጠቃልላል። የከተሞችን በአረንጓዴ በመሸፈን ኢትዮጵያ በብዙ ከተሞች ተንሰራፍቶ የቆየውን የአረንጓዴ መሰረተ ልማት አለመኖር ችግር ከመቅረፍ እንዲሁም የብክለትና የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ከመቀነስ ባሻገር በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች አኗኗርን ለማሻሻል አቅዳለች። ለዚህም ኢትዮጵያ በቅርቡ አስደናቂ የሆኑ ቦታዎችን በአረንጓዴ የመሸፈን ፕሮጀክቶችን አስጀምራለች። ከነዚህም ውስጥ በአዲስ አበባ የእንጦጦ ተራራ ፓርክ ና የወዳጅነት ፓርክን ለመጥቀስ ይቻላል። እንደዚህ ያሉ ፓርኮች ያለምንም ጥርጥር ከሀገር ውስጥና ከውጭ ቱሪዝም ከመጠቀም በተጨማሪ አረንጓዴ መሰረተ ልማቶች የመዘርጋት ዕድል ይፈጥራል።

ለ. **አካባቢን ከንክኪ መከለል**

አካባቢን ከንክኪ በመከለል የተጎዱ መሬቶችን እንዲያገግሙ ማስቻል ለብዙ አመታት በኢትዮጵያ ሲተገበር ቆይቷል። ተፈጥሮ ራሱን የሚተካበትን የተለመደ ሁኔታ በመከተል ደንና ሳር መልሰው በራሳቸው መንገድ እንዲበቅሉ የሚስችል ዘዴ ነው። በአሁኑ ወቅት ሀገሪቱ ይህንን ዘዴ በመከተል ከ3.5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት መሸፈን ችላለች። እንሰሳትና ተክሎች ከመጠበቅና የመሬት ምርታማነትን ከመጨመር ባሻገር የህብረተሰቡን የኑሮ ዘዴ ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። የእንሰሳት መኖ፣ የደንና የደን ያልሆኑ ውጤቶች እንደ ማርና ቅመማቅመም ያሉት ጠቀሜታዎች ከዚህ ውስጥ ይጠቀሳሉ።

ሐ. **አሳታፊ የደን አስተዳደር**

አሳታፊ የደን አስተዳደር በኢትዮጵያ የደን ጭፍጨፋን ለመቀነስ በሚል አላማ መተግበር ጀምሯል። አሳታፊ የደን አስተዳደር እ.አ.አ በ1994/5 ሲጀመር ሶስት አላማዎች የነበሩት ሲሆን እነዚህም የተወሰኑ የደን ባለቤትነት መብቶችን ከመንግስት ወደ ማህበረሰቡ ማውረድ፣ ለማህበረሰቡ የደን ሀብትን በዘላቂነት የማስተዳደርና ቀጣይነት ማረጋገጥ ሀላፊነት መስጠትና አግባብ ያልሆነ የደን ምርት አጠቃቀምን መቀነስ ናቸው።

አሳታፊ የደን አስተዳደር ለማህበረሰቡ የለት ገቢ እና የስርዐተ-ምህዳሩን አገልግሎት በማጠናከር በርካታ ተጨባጭ የሆኑ ጠቀሜታዎች እያስገኘ ይገኛል። አሳታፊ የደን አስተዳደር ለማህበረሰቡ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው ያስቻለ ሲሆን ከደንና የደን ካልሆኑ ውጤቶች የሚገኘውን ገቢም እንዲጨምር አድርጓል። በአሁኑ ወቅት የብሄራዊ ሬድ መርሃ ግብር በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዐት እየተተገበረ ይገኛል።

ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት በተጨማሪ ሀገሪቱ የተለያዩ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ የአየር ንበረት ለውጥ ማጣጣሚያ መፍትሄዎች ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ ትላልቅ ፕሮግራሞች ስትተገብር ቆይታለች። ከነዚህም ውስጥ የምርታማነት ሴፍቲኔት ፕሮግራም እና የግብርና ምርታማነት መጨመር ፕሮግራም ይጠቀሳሉ።

ተፈጥሮን መሰረት ላደረጉ መፍትሄዎች ትግበራ ፋይናንስ ማፈላለግ

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በ7 የኢኮኖሚ ዘርፎች 60 የሚሆኑ ተግባራትን የለየ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 13 የሚሆኑት በግብርናው ዘርፍ የተለዩ የማስተሰረያና የማጣጣሚያ ተግባራት ሲሆኑ 80 ፐርሰንቱ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ናቸው። የፋይናንስ ፍላጎትን በተመለከተ የደኑ ዘርፍ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ተግባራትን ለማከናወንና ሂላማዎችን ለማሳካት 7.9 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልገው ይገመታል።ለግብርና ማጠናከሪያና ለመስኖ ማስፋፊያ 30 ቢሊዮን ዶላር ሲያስፈልግ የእንሰሳቱ ዘርፍ 7.5 ቢሊዮን ዶላር ይፈልጋል። ስለዚህ በአጠቃላይ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎችን ለመተግበር እስከ 2030 እ.ኤ.አ 45.5 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋል። በተጨማሪም ታዳሽ ሀይልን ማመንጨት በርካታ መዋዕለ ንዋይ ይፈልጋል። በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ የሚገኘው ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ፋሲሊቲ ከሀገር ውስጥና ከአለም አቀፍ ከህዝብና ከግል ምንጭ እነዚህን ተግባራት ለመተግበር ገንዘብ ለማፈላለግና ተደራሽ ለማድረግ በሚል አላማ ተቋቁሟል።

ወደ ገፅ ፬

ከገፅ ፮ የቀጠለ..

ለስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ትግበራን እንደ ማስፋፍያ መንገድ

ከዚህ ቀደም በነበረው መልካም ተሞክሮ መሰረት ኢትዮጵያ የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ (PES) ስትራቴጂን ቀርፃለች። ስትራቴጂው የስርዐተ -ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ህግ ሊተገበር የሚችልበትን ማዕቀፍና የዘርፍ መ/ቤቶች የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ለመተግበር የሚቻልበትን መመሪያ እንዴት ሊያወጡ እንደሚችሉ ያስቀምጣል። ከዚህ በተጨማሪ የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የገንዘብ ምንጮችን፣ አስተዳደርና ገንዘቡ ከብሄራዊ አካውንት የስርዐተ-ምህዳር ጥበቃ ስራ ወደ ሚያከናውኑት ዘርፍ መ/ቤቶች እንዴት እንደሚፈስ አስቀምጧል።

እ.አ.አ በ2018 በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት መሰረት ኢትዮጵያ ከስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ በዓመት ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ የማግኘት አቅም እንዳላት የተገመተ ሲሆን ይህም ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ሀገር በቀል የሆነ የገንዘብ ምንጭ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ከተሰሩ የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ተሞክሮዎች የሚከተሉት ተስተውለዋል

- ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ልማት ስራዎቿን በመጠቀም የገንዘብ ምንጭ መፍጠር የምትችልበት ዕድል ሲኖራት ይህም ሀገሪቱ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ለመተግበር ያለባትን የገንዘብ እጥረት ከመቅረፍ አኳያ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

- የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የመሬት ማሻሻል ልማት የሚሰሩ ግለሰቦች ወደ ስርዐተ-ምህዳር ጥበቃ ለማምጣት ጠንካራ መሳሪያ ነው።

- በሀገር አቀፍ ደረጃ የስርዐተ-ምህዳር መመናመን የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ፍላጎት እንዲኖርና የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ፖሊሲና ፕሮግራም እንዲስፋፋ አድርጓል።

በአጭሩ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ተስፋፍቶ የመሬት መራቆትን ለመከላከል፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦችን አኗኗር ለመቀየር ያስችላል።

ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ትግበራ እየገጠሙት ያሉት ተግዳሮቶች

ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ትግበራ እየገጠሙት ያሉት ተግዳሮቶች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ያጠቃልላል፤

- ለትግበራውና ትግበራውን ለማስፋፋት የሚሆን በቂ ፋይናንስ አለመኖር። ለዚህ ተግዳሮት ዋና ምክንያትቶች ከአለም አቀፍ ተቋማት ሊገኝ የሚችለውን ገንዘብ መገመት አለመቻልና ለተገኙት ደግሞ ዝቅተኛ ፍሰት መኖሩ ነው፤

- የመንግስት ተቋማት ባለሙያዎች የመተግበር አቅም ዝቅተኛ መሆን፤

- ዕለታዊ የሆኑ ፍላጎቶችን ከማሳካት አኳያ ከአሳታፊ የደን አስተዳደር የሚገኘው ጠቀሜታ በረጅም ግዜ የሚታይ መሆኑና ከፍተኛ የመሬት መራቆት ለማገገም ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ መፈለጉ፤

- ከጥቂት ቦታዎች ላይ የሚገኘውን የግብርና ምርት ለመጨመር ቴክኖሎጂና ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎች አለመኖር፤

- የስርዐተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ፅንሰ-ሀሳብና ልምድ በባለሙያና በተቋም ደረጃ ዕውቅና እንዲያገኝና እንዲተገበር ጊዜ ማስፈለጉ፤

- የተለያዩ ፕሮግራሞች ትግበራ ላይ ተፅዕኖውን ያሳረፈው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ናቸው።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150

ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com

ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

ስራውን የደገፉ አካላት

NDC PARTNERSHIP | IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS OF DENMARK | Federal Ministry for Economic Cooperation and Development | Supported by: Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety | based on a decision of the German Bundestag | Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands | Norwegian Ministry of Climate and Environment | Norwegian Ministry of Foreign Affairs | Government Offices of Sweden Ministry for Foreign Affairs | UK Government

CDKN Climate & Development Knowledge Network | SOUTH SOUTH NORTH TOWARDS CLIMATE RESILIENCE | Funded by Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands | IDRC | CRDI International Development Research Centre Centre de recherches pour le développement international Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.